የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር 28
ጋራ ሚያዚያ 4 ቀን 1998 ዓ.ም ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት
ጠባቂነት የወጣ

9th year No 29
Samara- January, 2005

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ ሀብት ልማት ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ገጽ ----- 1

አዋጅ ቁጥር 28/1998 ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ለማቋቋሚያ የወጣ አዋጅ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ ሃብት አስተዳደር ልማት ለማሻሻልና ዘርፉ ለክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ሊያበረክት በሚችለው ሁኔታ እንዲጠናከር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 47/3/ሀ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ #አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ማቋቋሚያ/ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 28/1998; ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

በዚህ #አዋጅ; ውስጥ፦

1. #ክልል; ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነው።
2. #ቢሮ; ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ነው።
3. #ምክር ቤት; ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ነው።
4. #መንግስት; ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነው።

አንቀጽ 3

መቋቋም

1. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ /ከዚህ በኋላ #ቢሮ; የተባለ/ የሚጠራ ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው የመንግስት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ቢሮው ተጠሪነቱ በአርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል።

አንቀጽ 4

ዋና መስሪያ ቤት

የቢሮው ዋና መ/ቤት በሠመራ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላል።

አንቀጽ 5

ዓላማ

የቢሮው ዋና ዓላማ የክልሉን ውሃ ሃብት በማስተዳደር በማልማት ዘርፍ ለክልሉ ህዝብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩሉን አዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ ነው።

አንቀጽ 6

የቢሮው ስልጣንና ተግባራት

1. የክልሉን የውሃ ሃብት ማስተዳደር፣ የውሃ ተግባራዊነታቸውን መከታተል፣ የሀገሪቱን የውሃ ሃብት አስተዳደር ፖሊሲዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
2. በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የውሃ ሃብት ክምችት/አለኝታ/ ሥርጭትና አማራጮች ማጥናት፣ በመስኩ የምርምር ስራ ማከናወን፣
3. የውሃ ሃብት፣ የሃይድሮሊጂ፣ የሜቲሮሎጂ መረጃ አሰባሰብ መመሪኛ ስነ-ስርዓት መቅረጽ፣ መረጃዎቹን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ፣ያዝና እየተከታተሉ ወቅታዊ ማድረግ፣ ለአገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ፣ የሜታዴታ ቤዝ ማደራጀት፣
4. የመጠጥ፣ የውሃና ፍሳሽ እና የመስኖ ውሃ፣ አገልግሎት ዋጋዎችንና የታሪፍ ሃሳቦችን እያጠኑ ለመስተዳደር ም/ቤት ማቅረብ፣ በስራ ላይ ማዋል.
5. ክልላዊ ባህርይ ያላቸውን የመጠጥ ውሃ፣ የመስኖ የድሬኔጅ፣ የሳኒቴሽንና የተፋሰስ እንክብካቤ ፕሮጀክቶች የፊዚቢሊቲ ጥናትና የዲዛይን ሥራ ማካሄድ፣ የግናባታ ቁጥጥር ማከናወን፣ በባለቤትነት ማሠራት፣
6. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ውሃ ነክ የልማት ፕሮጀክቶች ቴክኒካዊ ግምገማ ማካሄድ፣ ሥራቸውን መቆጣጠር፣
7. ለመጠጥ ውሃና ለመስኖ ልማት ፈንድ ማፈላለግ፣ አጠቃቀሙን በበላይነት መቆጣጠር፣
8. ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን በክልሉና በተለይም በአርብቶ አደሩ ዘንድ የመስኖ እርሻናየመስኖ ግጦሽ ልማት እንዲለመድ የሚያበረታታ ስልት መቀየስ፣ ለዚህ የሚረዳ ፕሮግራሞችን መንደፍ፣ ተግባራዊነታቸውን መከታተል፣
9. ከመስኖ መሠረተ ልማት ጋር በተያያዘ ሊመጡ የሚችሉ የአካባቢ ተፅዕኖዎችን መከታተል፣ ሊከሰቱ የሚችሉ እንደ ውሃ ወለድ በሽታ፣ የውሃን አካባቢ ብክለትና የመሳሰሉ አደጋዎችን ለመቆጣጠር ከሚመለከታቸው ጋር መስራት፣
10. ለመስኖ ልማት ሥራ የተመቸ ተቋማዊ መሠረት እንዲዘረጋ፣ ህብረተሰብ፣ የግሉ ዘርፍና ሌሎች አካላት ሁሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትና አስተዋፅኦ የሚያደርጉበት ሁኔታ እንዲመቻች ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ስልት መቀየስ፣ ለተግባራዊነቱ መስራት፣
11. በክልሉ ውስጥ የግል ባለሃብ ቶች በመንግስት ደንብ መሰረት በመጠጥ ውሃ፣ የመስኖና ሳኒቴሽን እንዲሁም ተፋሰስ ልማት ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ማበረታታት፣ አቅጣጫ መምራት፣
12. በውሃ ተጠቅሞ የለማት ስራ ለመስራት፣ በውሃ ስራዎች አማካሪነት ለመስማራት፣ ፈቃድ መስጠት፣ መቆጣጠር፣
13. በውሃ ሃብት አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎ ማሳደጊየ ዘዴዎች ማጥናትና፣ ምክር መለገስ፣
14. በክልሉ የመጠጥ ውሃ፣ የመስኖ የሳኒቴሽን ድሬነጅ የተፋሰስ ልማት ተስማሚ ቴክኖሎጂ እድገት መሰረት እንዲይዝ ማጥናት፣ መመሪያ መቅረፅ፣ መከታተል፣
15. ለመንግስት የመጠጥ፣ መስኖ ሳኒቴሽንና ድሬነጅ እንዲሁም የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ ለፕሮጀክት አፈፃፀም መመሪያና የአሰራር ስነ-ስርዓት መቅረጽ፣ የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም መቆጣጠር፣

16. ለውሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤቶችና ለመጠጥ ውሃ፣ መስኖ ሳኒቴሽንና፣ ድሬኔጅ አገልግሎቶች የኦፕሬሽን፣ የሜንቴናንስ እና ማኔጀሪያል ድጋፍ መስጠት፣ ከጽ/ቤቱ አቅም በላይ የሆኑትን የጥገና ስራዎች መስራት ክልል አቀፍ የጥገና ስታንዳርድ መቅረጽ፣ በክልሉ የጥገና ስራ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን መከታተል፣
17. ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች ለሚውለው ውሃ የተወሰነው የጥራት ደረጃ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ፍሳሾች የተወሰነ የጤናማነት ደረጃ በክልሉ ውስጥ በስራ ላይ መዋልን መቆጣጠር፣
18. የክልሉን የሜትሮሎጂ አገልግሎት በበላይነት መምራት፣
19. መንግስታ ላልሆኑ ድረጅቶች ውሃ ነክ እንቅስቃሴዎ አቅጣጫ መስጠጥ፣
20. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የግንባታ ስራዎችን በባለቤትነት መስራት።

አንቀጽ 7

አደረጃጀት

ቢሮው፦

1. በክል ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልል ምክር ቤቱ የሚሾም አንድ የቢሮ ኃላፊ እንዲሁም፣
2. ለስራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች ይኖሩታል።

አንቀጽ 8

የቢሮ ኃላፊው ስልጣንና ተግባር

1. የቢሮው ኃላፊ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ የመሰረት የቢሮውን ስራዎ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቢሮ ኃላፊው

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የመለከቱትን የቢሮውን ተግባሮች በስራ ላይ ያውላል።

ለ/ በመንስት ሠራተኞች ህግ መሰረት የቢሮውን ሠራተኛ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ/ የቢሮውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል።

መ/ ለቢሮው በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል።

ሠ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ቢሮውን ይወክላል፣

ረ/ የቢሮውን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለአርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ያቀርባል።

ሰ/ የቢሮው ኃላፊው ለቢሮው የስራ ቅልጥፍና በሚስፈልገው መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለበታች ኃፊዎ በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

አንቀጽ 9

የምክትል ቢሮ ኃላፊ ስልጣንና ተግባር

- ለቢሮ ኃላፊው በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሰራል።
- ለቢሮ ኃፊው ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል።

አንቀጽ 11

ሂሳብ መዛግብት

1. ቢሮው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የቢሮው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ።

አንቀጽ 12

የተሻሩ ህጎች

1. የአፋር በሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሃብት ልማት ቢሮ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 15/1994 አንቀጽ 18 በዚህ አዋጅ ተሸሯል፣
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ወይም በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን የሚመለከት ማንኛውም ህግ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ 13

<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአፋር ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ--------- ቀን 1998 ዓ.ም

አስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር